## የአሰራር ስልት

አሰሪና ሰራተኛን በተፈለገው ደረጃ ማቀራረብ የማዕከሉ የውጤት መለኪያው ነው፡፡

አሁን ባለበት ሁኔታ ማዕከሉ አሠሪው ብቃት ያላቸውን የሥራ ፈላጊዎች ያመላክታል፡፡

የስራ ፈላጊዎች ማጣራት በአሰሪዎች ይከናወናል፡፡ ማዕከሉ የእጩዎችን ክህሎትና ልማድ እና የአሠሪዎችን የተለየ ፍላጎት ለማጣጣም ሁልጊዜ ጥረት ያደርጋል፡፡

## አስተዳደራዊ መዋቅር

- የወጣቶች የሥራ ቅጥር ማዕከል  በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ፣ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ቢሮ ፣ የወጣቶች እና ስፖርት ጉዳዮች ቢሮና ፣  በኢትዮጵያ ንግድ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ባህር ዳር ቅርንጫፍ እንዲሁም በአማራ አሰሪዎች ፌዴሬሽን የጋራ ትብብር የሚከናወን ፕሮጀክት ነው ፡፡

- የዓለም አቀፉ የስራ  ድርጅት (አይ. ኤል. ኦ.) “ትኩረት በመሰረታዊ የስደት መንስኤዎች ላይ በኢትዮጵያ ” የተሰኘው ፕሮጀክት አካል በመሆኑ የሙያና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

- ይህ ፕሮጀክት ከአውሮፓ ህብረት ልማት ፈንድ ለአፍሪካ ከተባለው ድርጅት በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ እና አዲስ አበባ በሚገኘው የኢጣሊያ ኤምባሲ አስተዳዳሪነት የሚከናወን የሲንስ (SINCE) ፕሮግራም አካል ነው፡፡


ለበለጠ መረጃ

ወ/ሮ እመቤት መንገሻ ፣
የ ወጣቶች የስራ ቅጥር ማዕከል አስተባባሪ
0582221750 (የመስመር)
ባህር ዳር ፣ ቀበሌ 14


የ ወጣቶች የስራ ቅጥር ማዕከልን (YES CENTER) ይጎብኙ!!!

Embassy of Italy Addis Ababa

Funded by the European Union

# YES CENTER
Youth Employability Services

# የወጣቶች የሥራ ቅጥር ማዕከል




... በአገልግሎት ሰጭነቱ ብቁ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ ፤ አሰሪና ሰራተኛን የሚያገናኝ የወጣቶች የሥራ ቅጥር ማዕከልነው፡፡

### ሥራ ፈላጊ ወጣቶች

. አባል ሁኑ!

. ተመዝገቡ!

. ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያን ተከታተሉ !

### አሠሪዎች/ቀጣሪዎች

. ክፍት የሥራ እንዳለዎ ይንገሩን!
. የክህሎት ማበልፀጊያ ስልጠናዎች በጋራ ያዘጋጁ!
. አሰሪና ሰራተኛን የማገናኛ ኤግዚቢሽን  ያዘጋጁ!
. ያማክሩን!

## መግቢያ

የዓለም አቀፉ የስራ ድርጅት (አይ. ኤል. ኦ.) “ትኩረት በመሰረታዊ የስደት መንስኤዎች ላይ በኢትዮጵያ” የተባለውን ፕሮጄክት በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ፕሮጄክቱ ሲንስ / SINCE / ተብሎ በሚጠራው በሰሜን እና መካካለኛዉ ኢትዮጵያ የሚታየውን ፍሰት ቅነሳ ፕሮጄክት አካል ነዉ፡፡

የሲንስ መርሃ-ግብር የሚከናወነው ከአውሮፓ ህብረት ልማት ፈንድ ለአፍሪካ ከተባለው ድርጅት በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ አዲስ አበባ በሚገኘው የኢጣሊያ ኤምባሲ በኩል የሚተገበር ሲሆን አላማውም በሰሜን እና መካካለኛዉ ኢትዮጵያ ፤ ለአደጋ በእጅጉ ተጋላጭ የሆኑ የኑሮ ሁኔታዎችን የሚመሩ የማሕበረሰብ ክፍሎችን የአኗኗር ሁኔታ ማሻሻልን ያደረገ ሲሆን መርሃ-ግብሩ ለስደት ተጋላጭ እና ከስደት ተመላሾችንም ያካትታል፡፡

የትኩረት አቅጣጫውን ያልተገባ የስደተኞች ፍሰትን መግታት ላይ ያደረገው ይህ “ ትኩረት በመሰረታዊ የስደት መንስኤዎች ላይ በኢትዮጵያ ” የተሰኘው ፕሮጄክት የተለያዩ የስራ እድሎችን ማፈላለግን ጨምሮ ለኑሮ ምቹ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ለወጣቶች መፍጠርን አላማው ያደረገ ፕሮጄክት ነው፡፡ ይህ ፕሮጄክት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ በአማራ ፣ በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች ፣ የገጠር ከተሞች እና ከተማ አካባቢ የሚገኙ ሥራ አጥ ወጣቶችን ፣ የዩኒቨርሲቲ ብሎም የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተመራቂ ወጣቶችን እና ለስደት ተጋላጭ የሆኑትን የማሕበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰራ ፕሮጄክት ነው፡፡ በመሆኑም ፕሮጄክቱ በአሁን ጊዜ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባህርዳር ከተማ ላይ በአገልግሎት ሰጭነቱ ብቁ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ ፤ አሰሪና ሰራተኛን የሚያገናኝ የወጣት የቅጥር አገልግሎት የሙከራ ማዕከል ከፍቷል፡፡

## ዓላማ

ይህ የሙከራ ማዕከል ለወጣቶች ምቹ የሆነ የስልጠና ፣ የመላማመጃና የስራ ምደባ ሁኔታዎችን ያረጋግጣል፡፡

ለስራ ፈላጊዎች የአሰራር መንገድ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎ ሳያሰልስ ይሰጣል፡፡ የስራ ፈላጊ እና በገበያ መካከል ባሉ ጉዳዮች ፤ በክልሉን ሆነ በፌደራል ደረጃ የስራ ስምሪት እድሎች እና የስራ ገበያ ፍላጎት መረጃ በመሆን ያገለግላል፡፡

በግል ድርጅቶች ፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከልም መልካም ትስስርን ይፈጥራል፡፡ የሰራተኛና የስራ ልምድ ልውውጥ ከማድረግ አልፎ ሰራተኛን በብዛት ለማግኘት አጋጣሚዎችን ያመቻቻል፡፡



## ተጠቃሚዎች

- ሥራ ፈላጊ ወጣቶች
- የኮሌጅ / ዩኒቨርሲቲ ምሩቃን
- ከስደት ተመላሽ ወጣቶች
- አሠሪዎች/ቀጣሪዎች
- ትምህርት ያቋረጡ ወጣቶች

## ዋና ዋና አገልግሎቶች

### ለሥራ ፈላጊ ወጣቶች

- ነፃ የምዝገባ አገልግሎት
- ነጻ የሙያ ምክር አገልግሎት
- ለወጣቶች ስራ ሊያገኙ የሚችሉበትን የስራ ባዛር እንዲሳተፉ ዕድል መፍጠር
- ወጣቶችን የተግባር ላይ ልምምድ ተመድበው እንዲሰሩ ማገናኘት
- ወጣቶች የተሻለ አቅም ያላቸውን ቀጣሪ ድርጅቶች የሚያገኙበትን እድል መፍጠር
- መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል ሊገኙ በሚችሉ ማንኛውም የቅጥር ዕድሎች በመፍጠር በልዩ ሁኔታ ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ፡፡
- የሥራ ስምሪት ዕድሎች እና የሥራ ገበያ ፍላጎት መረጃ በክልልም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ማቅረብ፡፡
- በግል እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መካካል ወጣቶችን በግል የስራ ፈጠራ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስተሳሰር፡፡

### ለአሠሪዎች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት

- ለተለያዩ አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች እንደ ሁነኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች (BOLSA), ፣ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ልማት ቢሮ (TVED) ፣ የፖሊቴክኒክ እና የሙያ ኮሌጆች እንዲሁም ሌሎች በአካባው የሚገኙ አግባብነት ያላቸው አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ያገለግላል፡፡
- በሙያዊ ተመርጠው እና ዝርዝር መረጃ ያላቸው ወጣት ሙያተኞችን ያገኛሉ፡፡
- ለክፍት የስራ ቦታዎች ዝግጁ የሆኑ እጩ ተቀጣሪ ወጣቶችን ያቀርባል፡፡